የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0795/17
ቀን/Date ሰኔ 09 2017

ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

ባሉበት

ጉዳዩ ፡- <u>የቅድመ ግብር (Withholding tax) ክፍያን ይመለከታል</u>፤

ዕቃ ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ወቅት በጉምሩክ ስጋት ስራ አመራር መርህ መሠረት በዝቅተኛ ወይም በመካከለኛ የስጋት ደረጃ በመስተናገዱ ወይም ሌሎች ምክንያቶች በዕቃው ላይ የቅድመ ግብር /Withholding tax/ ክፍያ መክፈል እያለበት ሳይከፍል ከገባ በኋላ በጉምሩክ ድህረ ዕቃ አወጣጥ አዲት በኩል ይኸው ክፍያ መኖሩ ተረጋግጦ ለአስመጪዎች ክፍያውን እንዲፈጽሙ በሚጠየቁበት ጊዜ ዕቃው በገባበት ወቅት ለጉምሩክ ያልተከፈለ ቢሆንም ግብር ለሚከፍሉበት መስሪያ ቤት በዓመታዊ ትርፍ ግብር ላይ ተካቶ የተከፈለ በመሆኑ በድጋሚ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ለኮሚሽኑ ተደጋጋሚ ቅሬታ በማቅረባቸው ምክንያት በዚህ ጉዳይ ላይ ኮሚሽኑ ሊከተለው የሚገባው የኦዲት አሰራር ምን መሆን እንዳለበት በቁጥር 4/0908/16 ሰኔ 22 ቀን 2016 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ለገቢዎች ሚኒስቴር ተጠይቆ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡

በዚሁ መሠረት የገቢዎች ሚኒስቴር በቁጥር 3.1/98/17 ነሐሴ 24 ቀን 2016 ዓ/ም በሰጠው ዝርዝር ማብራሪያ ላይ፡-

1. በገቢ ግብር ህጉ ድንጋጌ መሰረት ዕቃው ወደ ሀገር በገባበት የግብር ዓመት የንግድ ስራ ግብር ሪፖርት ተደርጎ ያልተከፈለ ከሆነ በድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት ጊዜ ቅድመ ግብሩ ወለዱን ጨምሮ መከፈል አለበት፤
2. የድህረ ዕቃ አወጣጥ አዲት የተደረገው፤ ዕቃው በገባበት የግብር ዘመን ያለው የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ሪፖርት ተደርጎ ከተከፈለ በኋላ ከሆነ በግብር ህጉ መሰረት ሊካካስ ስለማይችል ቅድመ ግብሩ የሚከፈል አይሆንም፡፡ ነገር ግን ዕቃው

ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር እንዲሰፍን ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ወደ ሀገር ከገባበት ቀን እስከ የግብር ዘመኑ የንግድ ስራ ግብር እስከተከፈለበት (የሚከፈል ከሌለም ሪፖርት እስከተደረገበት) ቀን ድረስ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 37 መሰረት ወለድ ሊከፈል ይገባል፤

3. በጉምሩክ በኩል የ3% (የሶስት በመቶ) ቅድመ-ግብር ውሳኔ ለመስጠት እና በድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት መሠረት የሚገኘው ግኝት በአስመጪው ላይ በሀገር ውስጥ ታክስ በኩል ሊያስከትል የሚችለውን ኃላፊነት በተገቢው ህግና አሰራር ተግባራዊ እንዲሆን የአዲት ግኝቱ የተገኘበት ታክስ ከፋይ ከተመዘገበበት ቅ/ጽ/ቤት ተገቢውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት የሚያስፈልግ ሲሆን አሰራሩ እስኪዘረጋ ከሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይገባል በማለት ይገልፃል።

በማብራሪያው ላይ የግብር ዓመት ወይም ዘመን በሚል የተገለጸው በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም የሚኖረው መሆኑ ታዉቆ በማንኛውም ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቅድመ ግብር ክፍያ ሳይከፈል የገባ መሆኑ በድህረ ዕቃ አወጣጥ አዲት የተረጋገጠ እንደሆነ ዕቃው ወደ አገር የገባበት /ትራንዚት ያጠናቀቀበት/ ቀን ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 በተገለጸው አግባብ ከግብር ዘመኑ ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ እንዲፈጸም፤ የተሰጠው ማብራሪያ የሚመለከተው ዕቃ ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ የቅድመ ግብር ክፍያ መክፈል ሲገባው የጉምሩክ ፕሮሲጀር ኮድ በትክክል ባለመሙላት ምክንያት ሳይከፍል እንዲገባ የተደረገን ዕቃ ብቻ ሲሆን በማብራሪያው ተራ ቁጥር 3 ላይ የተገለጸው አሰራር እስኪዘረጋ ድረስ በዚሁ ጉዳይ ላይ የሚከናወን አዲት ከአዲት ውሳኔ በፊት አዲት በተደረጉት ዲክላራሲዮኖች ተመዝግበው የገቡ ዕቃዎቸው ላይ የቅድመ ግብር ክፍያን በተመለከተ ግብር ከፋዩ ግብር ከሚከፍልበት መስሪያ ቤት ማስረጃዎች ተሟልቶ እንዲቀርብ ማድረግ እንዲሁም በዚሁ መሰረት በጉምሩክ በኩል የተሰበሰበ ክፍያ ግብር ለሚከፍሉበት መስሪያ ቤት ማሳወቅ የሚገባ መሆኑን እያሳሰብኩ፤ የተሰጠው ማብራሪያ 4 ገጽ ኮፒ ተያይዞ ተልኳል።

ከሰላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ግልባጭ//

- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ አዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት

ጉምሩክ ኮሚሽን

ቀን Date ነሐሴ 2 4 2016
ቁጥር Ref.No. ኢ.ገ/98/17

ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ቅድመ-ግብር ክፍያን በተመለከተ የተሰጠ ማብራሪያ፤

የጉምሩክ ኮሚሽን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ቅድመ ግብር ክፍያ እንዲከፍሉ ግዴታ የተጣለባቸው አስመጪዎች የጉምሩክ አገልግሎት የሚሰጠው የስጋት ስራ አመራር መርህን መሰረት በማድረግ በመሆኑ እና በሌሎች ምክንያቶች የአንድ የግብር ዘመን ካለፈ በኋላ በድህረ ዕቃ አወጣጥ አዲት ሲረጋገጥ የቅድመ ግብር ክፍያ ሊጠየቅ ይገባል ወይስ አይገባም እንዲሁም ኮሚሽኑ በዚህ ረገድ ሊከተል የሚገባውን የአዲት አሰራር ምን መሆን አለበት በማለት ሰኔ 22 ቀን 2016 ዓ/ም በቁጥር 4/0908/16 በተጻፈ ደብዳቤ ማብራሪያ እንዲሰጣችሁ መጠየቁ ይታወሳል።

የተያዘው ጭብጥ፤

በድህረ ዕቃ አወጣጥ አዲት በሚደረግበት ወቅት የቅድመ ግብር ክፍያ ሊጠየቅ ይገባል ወይስ አይገባም እንዲሁም ወደፊት ኮሚሽኑ ድህረ ዕቃ አወጣጥ አዲት ሲያደርግ ቅድመ-ግብር ክፍያ በተመለከተ ሊከተል የሚገባውን የአዲት አሰራር ምን መሆን አለበት የሚል ነው።

ተገቢነት ያላቸው ህጎች፤

- የፌዴ ራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006
- የፌዴራል ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008
- የፌደራል ገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009


የተሰጠው ማብራሪያ፤

ከላይ ለተገለጸው ጭብጥ የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የሰጠውን የህግ አስተያየት መነሻ በማድረግ በቀን 27/11/2016 ዓ.ም በቁጥር 3.1/47/17 በተጻፈ ደብዳቤ የህግ አስተያየቱን በማያያዝ ምላሽ መላኩ ይታወሳል። ለቀረበው ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ሕህግ አገልግሎት ዳይሬክተር እና ለሚኒስትር አማካሪዎች ጉዳዩ ተመርቶ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የተሰጠውን አስተያየት መነሻ በማድረግ ተቋማዊ መልስ መስጠት ሲገባ አንደኛውን አስተያየት አባሪ አድርጎ በመላክ ምላሽ የተሰጠ ስለሆነ በድጋሚ ማብራሪያ መሰጠት እንዳለበት ታምኖበታል።

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 121 እና 122 መሰረት በሚደረግ የድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት በጉምሩክ የሥነ-ሥርዓት ሂደት ሊከፈል ሲገባው ሳይከፈል የቀረን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማስከፈል የሚቻል ስለመሆኑ ተደንግጓል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሊከፈል ሲገባው ሳይከፈል የቀረን ቀረጥና ታክስ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚደረግ ደህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት ማስከፈል የሚቻል ቢሆንም ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የሚከፈለው የ 3 % (የሶስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ቅድመ ግብር ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ትግበራ በተከናወነበት የግብር ዓመት ከግብር ከፋዩ ላይ ከሚፈለገው ዓመታዊ የንግድ ስራ ግብር ዕዳ ጋር ስለሚካካስ የዓመታዊ የንግድ ስራ ግብር ማስታወቂያ አቅርቦ መከፈል ወይም አለመከፈል በድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት ወቅት የቅድመ ግብር ውሳኔ ይወሰን ወይስ አይወሰን ለሚለው ምላሽ ይፈልጋል።

ከዚህ በፊት በተሰጠው አስተያየት እንደተገለጸው የ 3 % (የሶስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ቅድመ ግብር፤ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ሊከፍለው ከሚገባው ዓመታዊ የንግድ ስራ ገቢ ግብር ጋር ሊካካስ የሚገባው የቅድመ-ግብር ክፍያ በቀጥታ መወሰን አለበት ወይስ ታክስ ከፋዩ በተጠቀሰው የግብር ዘመን ውስጥ ሊከፍለው ከሚገባው የንግድ ስራ ገቢ ግብር ጋር በማገናዘብ መወሰን አለበት የሚለው ድህረ ዕቃ አውጣጥ አዲቱ የተደረገበት ጊዜ የሚወስነው ይሆናል። ምክንያቱም ድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲቱ የተደረገው የግብር ዘመኑ የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ሪፖርት ተደርጎ ከተከፈለ በኋላ ወይም በፊት መሆኑ በቅድመ ግብሩ አከፋፈል ላይ ያለው ውጤት የተለያየ ነው።





በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 85(1) መሰረት ዕቃዎች ወደ ሀገር ሲገቡ 3 % (የሶስት በመቶ) የንግድ ስራ ገቢ ግብር በቅድሚያ ለባለስልጣኑ እንዲሚከፈል እና ቅድመ-ግብሩ በግብር ዘመኑ የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ጋር የሚካካስ ስለመሆኑ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 85(2) ላይ ተደንግጓል።

በተያዘው ጉዳይ ላይ የተጠየቀው ጥያቄ ዕቃዎች ሲገቡ ሳይሆን ከገቡ በኋላ በሚደረግ የድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት ሲካሄድ በሚገኝ ልዩነት ላይ ስለሚከፈል ቅድመ ግብር ነው። የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 64 ግብር ቀንሶ ለባለስልጣኑ የማስተላፍ ግዴታ የተጣለበት ሰው ግዴታውን ያልተወጣ ቢሆንም ግብር ከፋዩ ግብሩን የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ የአዋጁ አንቀጽ 97(3) (ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ቀንሶ ካልያዘ ወይም ቀንሶ የያዘውን ያልከፈለ ለታክስ ባለስልጣኑ የመክፈል እንዳለበት የተደነገገው) ተፈጻሚ እንደማይሆንበት ሰፍሯል። ስለዚህ በሀገር ውስጥ ግብይት ወቅት በዚህ አግባብ እንዲስተናገድ የተፈቀደ መሆኑ ለንግድ ስራ ከውጭ ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 85(1) መሰረት ዕቃዎች ወደ ሀገር ሲገቡ 3 % (የሶስት በመቶ) የንግድ ስራ ገቢ ግብር በቅድሚያ ለባለስልጣኑ እንዲሚከፈል ከተደነገገው አንጻር ሲታይ የግብር ዘመኑ የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቂያ ከቀረበና የሚፈለግ ግብር ከተከፈለ በኃላ መወሰን አለመወሰን በህጉ በግልጽ ያልተመላከተ ቢሆንም በቅድሚያ የሚከፈል ክፍያ ከመሆኑ አንጻር መታየት ይኖርበታል።

ከላይ በዝርዝር የተገለጸው የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የሚከተለው ማብራሪያ ተሰጥቷል።

ስለሆነም፡-

1. በገቢ ግብር ህጉ ድንጋጌ መሰረት ዕቃው ወደ ሀገር በገባበት የግብር ዓመት የንግድ ስራ ግብር ሪፖርት ተደርጎ ያልተከፈለ ከሆነ በድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት ጊዜ ቅድመ ግብሩ ወለዱን ጨምሮ መከፈል አለበት፤
2. የድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት የተደረገው፤ ዕቃው በገባበት የግብር ዘመን ያለው የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ሪፖርት ተደርጎ ከተከፈለ በኋላ ከሆነ በግብር ህጉ መሰረት ሊካካስ ስለማይችል ቅድመ ግብሩ የሚከፈል አይሆንም። ነገር ግን ዕቃው ወደ ሀገር ከገባበት ቀን እስከ የግብር ዘመኑ የንግድ ስራ ግብር እስከተከፈለበት (የሚከፈል ከሌለም ሪፖርት

አስከተደረገበት) ቀን ድረስ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 37 መሰረት ወለድ ሊከፈል ይገባል፤

3. በጉምሩክ በኩል የ3 % (የሶስት በመቶ) ቅድመ-ግብር ውሳኔ ለመስጠት እና በድህረ-ዕቃ አወጣጥ አዲት መሰረት የሚቆኘው ግኝት በአስመጪው ላይ በሀገር ውስጥ ታክስ በኩል ሊያስከትል የሚችለውን ታላቁነት በተገቢው ህግና አሰራር ተግባራዊ እንዲሆን የኦዲት ግኝቱ የተገኘበት ታክስ ከፋይ ከተመዘገበበት ቅ/ጽ/ቤት ተገቢውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት የሚያስፈልግ ሲሆን አሰራሩ እስከዘረጋ ከሚመለከተውን ቅ/ጽ/ቤት ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይገባል፤

በማለት ይህ ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን ቀደም ሲል በ 27/11/2016 ዓ.ም በቁጥር 3.1/47/17 በተጻፈ ደብዳቤ በዚህ የተተካ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ያሬድ ፈቃደ ፍሰሃ
የታክስ ማስታወቅ
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ

ገቢዎች ሚኒስትር